# <u>የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት መመሪያ ቁጥር 1026/2017 አጭር ማብራሪያ</u>

## 1. <u>ዳራ</u>

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ለውጭ ምንዛሪ ግኝት 18 በመቶ የሚያበረክቱ ሲሆን በግብይት ሂደት ዉስጥ ዘርፎቹ የስራ እድል በመፍጠር ረገድ ያላቸዉ ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡መንግስት የወጪ ንግዱን በማስፋፋት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የሚያጠናክር ቀልጣፋ ስርዓት እንዲፈጠር የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች ከመዘርጋት ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ከማቋቋም ጀምሮ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

ባለፉት አመታት የወጪ ንግድ ስርአቱን ለማሻሻል የተተገበሩ የአሰራር ለውጦች ባስገኙት ጠቀሜታ መሰረት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ተሞክሮአቸውም እንዲስፋፋና እንዲተገበር በማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ያስከተሏቸው ተፅዕኖዎች ተለይተዉና ተገምግመዉ ወቅቱ በሚፈልገዉ መሰረት የማሻሻያ እርምጃ መዉሰድ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ከግብይት እና እስከ ወጪ ንግድ ባሉት ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የግብይት ስርዓቱ ማነቆዎችን በመለየት ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሰረተ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ከምርት ገበያ ግብይት ስርዓት ጋር ትይዩ የሆነ አማራጭ የግብይት ስርዓት በወቅቱ በመዘርጋት በግብይት ሰንሰለቱ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ አቅም ያላቸዉን የወጪ ምርቶች በሚፈለገዉ ልክ ለገበያ በማቅረብ የሀገሪቱን የንግድ ሚዛን ጉድለት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት በቀጣይ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ በመሆን ያለንን የገበያ ድርሻ ለማስጠበቅና ለማሳደግ ተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታዎች ለማስተዋወቅ፣ አዲስ ገበያ ሰብሮ ለመግባት፣ የሌሎች ተመሳሳይ ምርት አምራች አገራት ዋጋዎችና አዝማሚያዎች እና የግብይት ወጪ ታሳቢዎችን በማድረግ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት ገበያዉ በሚፈልገው መጠን፣ ጥራት እና እንደየ ሀገራቱ ፍላጎት ከወቅቱ ጋር የተጣጣመና የተናበበ የግብይት እሴት ሰንሰለቱን የማዘመን፤ ቀልጣፋና ህጋዊ የማድረግ ስራ መከናወን ይኖርበታል፡፡

በዚህም የሚስተዋለዉን የተዛባ የንግድ ውድድር ሜዳ ተጨማሪ የግብይት አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ከምርት ገበያ ግብይት ጋር እኩል የግብይት መድረክ በመፍጠር ሁለት እና ከዚያ

በላይ አማራጭ የአሰራር ስርዓት በተዘረጋላቸዉ ቡናን በመሳሰሉ የወጪ ምርቶች የተመዘገበዉ የወጪ ምንዛሪ ገቢ ግኝት ዉጤት እንደ መልካም ማሳያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንን መልካም ተሞክሮበማስፋት የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች አማራጭ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋትየሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

## 2. <u>የቀጥታ ግብይት አሰራር ስርዓት</u>

ረጅም የግብይት የእሴት ሰንሰለት ለምርት ብክነትና የጥራት መጓደል፤ ህገ ወጥ ግብይት እና ኮንትሮባንድ መስፋፋት፤ ምርትን በክምችት መደበቅ ለመሳሰሉት ችግሮች የሚዳርግ መሆኑ በተሞክሮ ተስተውሏል፡፡ ይህም በውጭ ንግድ አፈጻጸማችን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት በቅባት እህሎች እና በጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት አሰራር ስርዓት መዘርጋት እንደ አንድ መፍትሄ ተወስዷል፡፡ ይህ የአሰራር ሥርዓት የግብይት ወጪን ይቀንሳል፤ ጊዜ ይቆጥባል እና የምርት ዱካን መሰረት ያደረገ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ምርት በጥራት እና በመጠን ማሳደግ እንዲቻል ተጠቃሚው እጅ እስኪደርስ ያለውን የእሴት ሰንሰለት የማዘመንና የግብይት ሥርዐቱ አቅራቢዎችን፣ ላኪዎችን እና ገዢ ሀገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር ይሆናል፡፡ ይህ የአሰራር ሥርዓት በቀጣይ ዓመታት የውጭ ንግድ አፈጻጸማችንን በማሳደግ የሀገሪቱን የልማት ግቦች ለማሳካት ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው ታምኖበታል፡፡

## 3. <u>የመመሪያዉ አስፈላጊነት፤</u>

- ረቂቅ መመሪያዉ የተዘጋጀው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ዘርፍ
- ግብይቱ ለህገወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ ያልተጋለጠ፣የተሳለጠ፤ጊዜ ቆጣቢና ወጪ የቀነሰና በቀጣይነት በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል አማራጭ የግብይት ስርዓት ለመዘርጋት በማስፈለጉ ሲሆን የሚከተሉትን ዓላማዎችን ለማሳካት ነው፡፡
- በዘላቂነት በአለም አቀፍ ገበያ በጊዜ፤ በመጠን እና በጥራት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፤

- የተንዛዛ  ግብይትን እና አላስፈላጊ የሆኑ የደላላ ጣልቃ ገብነትን ለመከላከል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ከዘርፉ የሚገኘዉን የወጪ ምንዛሪ ገቢ ማሳደግ፤
- የቅባት እና የጥራጥሬ ዘርፎች ኤክስፖርት ንግድ በራሱ አትራፊ እና አዋጪ ዘርፍ እንዲሆን ማስቻል፤
- ከምርት ብክነትና የጥራት መጓደል ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመቀነስ የምርት ዱካን መሰረት ያደረገ በጥራትና ብዛት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ማሳደግ፤
- በዘርፉ የተሰማሩ የግብይት ተዋኒያንን እና የሀገርን ጥቅም ማረጋገጥ፤
- በአጠቃላይ የግብይት እሴት ሰንሰለቱን አጭር፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ ማድረግ፡፡

## 4. <u>የመመሪያዉ የዝግጅት ሂደት፤</u>

- ✓ የዚህ መመሪያ ዝግጅት አጋዥ የሆኑ ባለፉት አመታት የግብይት ሥርዓቱን ከመሠረቱ በመለወጥ ዘመናዊና ቀልጣፋ የዕሴት ሰንሰለት ለመፍጠር የሚረዱ አሰራሮችን ለመተግበር በዘርፉ ላይ ሁለት ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡
- ✓ የመጀመሪያው በወጪ ምርቶች ግብይት ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ያተኮረ ጥናት ሲሆን፤
- ✓ ሁለተኛው ደግሞ በምርት ገበያው አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሚስተዋሉ ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡
- ✓ ከዚህ በመነሳት ረቂቅ መመሪያው ተዘጋጅቶ በባለሙያዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ የሥራ አመራር ደረጃ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡
- ✓ ሀምሌ 8 ቀን 2016 ዓ.ም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማናጅመንት አባላት በረቂቅ መመሪያው ላይ ዉይይት ተደርጎ አስተያየት ተሰጥቶበት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡
- ✓ ነሀሴ 9 ቀን 2016 ዓ.ም የግብይት ተዋንያን እና የባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ በማዘጋጀት  በረቂቅ መመሪያው ላይ ዉይይት ተደርጎ በተሰጡት አስተያየቶች መሠረት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡

## 5. <u>የመመሪያዉ ይዘት</u>

ረቂቅ መመሪያዉ በአራት ክፍሎች ሥር የተካተቱ 20 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን በየክፍሉ ሽፋን የተሰጣቸው ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የመጀመሪያው ክፍል ከአንቀጽ 1 እስከ 3 ባሉት ድንጋጌዎች የረቂቅ መመሪያዉን አጭር ርዕስ፣ ግልጽ ትርጉም የሚሹ ቃላት ትርጓሜዎችን እና የተፈጻሚነት ወሰንን የሚመለከቱ አንቀጾችን ያካተተ ነዉ፡፡
- ክፍል ሁለት ከአንቀጽ 4 እስከ 8 የቀጥታ ግብይት የአሰራር ስርዓትን የያዘ ሲሆን የቀጥታ ግብይት ትስስር ስለመፍጠር፣ ትስስሩ ስለሚፈጠርበት ውል ይዘት፣ ስለምርት ርክክብ፣ የክፍያ ሥርዓት፣ እና በቀጥታ ግብይት ስለሚሳተፉ አቅራቢዎች እና ላኪዎች ግዴታ በዝርዝር እንዲካተት ተደርጓል፡፡
- በክፍል ሦስት ደግሞ ከአንቀጽ 9 እስከ 13 ለቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች የተደነገገ ሲሆን ምርት የማጓጓዝ፣ የማዘጋጀት፣ በማከማቻ መጋዘን ስለማቆየት፣ ስለሚዛን እና ስለሽኘት አገልግሎት በዝርዝር ተካቷል፡፡
- በክፍል አራት ከአንቀጽ 14 እስከ 20 ድረስ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን በቀጥታ ግብይት ሥርዓት ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶች፣ ስለአስተዳደራዊ እርምጃዎች፣ ስለቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት እና ዉሳኔ አሰጣጥ፣ የመተባበር ግዴታ፤ ተፈጻሚነት ስለሌላቸዉ መመሪያዎች እና መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን አስፈላጊውን ጥናት በማካሄድ፣ ሌሎች ህጎችን መነሻ በማድረግ እንዲሁም ተከታታይ የምክክር መድረኮችን በማመቻቸት ይህን ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀትና በግብይት ተዋንያንና በባለድርሻ አካላት ውይይት አስተያየት እንዲዳብር በማድረግ በመጨረሻም በፍትህ ሚኒስቴር በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት በመከለስ መመሪያውን አጽድቆ ያቀረበ ስለሆነ ወደ ሥራ መግባት እንዲችል በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት እንዲመዘገብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡